# ያማርኛ ሕዝባዊ ሥነ ግጥም - ለአብነት ያህል

ደበበ ሰይፉ

የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዘመናት ውስጥ ያካበቱት ሰፊ የቃል ሥነ ጽሑፍ ቅርስ አላቸው ። ሕዝባዊ ሥነ ግጥም የዚህ ቅርስ አንድ ዐቢይ ገጽ ነው ። ሕዝባዊ ሥነ ግጥም እንደማንኛውም ሕዝባዊ ጥበብ ሁሉ የወጣበትን ማኅበረሰብ ቀለም ይይዛል ። የሰረጸበትን ዐውድ ምንነት ያንጸባርቃል ። ደምሳሳ በሆነም መንገድ እንኳን ቢሆን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የምንጠቅሳቸው የአማርኛ ሕዝባዊ ግጥሞች ፣ በተገጠሙበት ወቅት የነበሩትን ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን ይስላሉ ። ማኅበረሰባዊ ሂደቶችንና ክስተቶችንም ይገልጻሉ ። የኢትዮጵያ ሕዝ ቦች /የተለያዩ ብሔረሰቦች አባላት/ ያለፉባቸው የታሪክ እርከኖች ተሞላ ጐደል ተመሣሣይ በመሆናቸው ሳቢያ ሕዝባዊ ሥነ ግጥሞቻ ቸውም በቅርጽ ሳይሆን በይዘት አያሌ መቀራረቦችን እንደሚያሳዩ ግልጽ ነው ። ይህንንም ያስተዋለውም አንድ ምሁር የአማርኛን ሕዝባዊ ሥነግጥም ሰብስቦ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ሥነግጥም ማለቱ በዚህም ምክንያት ሣይሆን አይቀርም ። (1) እኛም እዚህ ያማርኛ ሕዝባዊ ሥነ ግጥም ስንል ይዘቱ ተካቶ የተከሠተበትን ቋንቋ መሠረት በማድረግ እንጂ ፤ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የማይጋሩት ሀብት ነው በሚል መነሻ አይደለም ።

ሕዝባዊ ሥነ ግጥም በሕዝብ አንደበት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የሚቆይ እንጂ እንደተደረሰ በወረቀት ላይ የሚሰፍር ጥበብ ባለመሆኑ ፤ ለተመራማርያን አንዳንድ አነስተኛ ችግሮችን መፍጠሩ አልቀረም ። የመጀመሪያው ችግር የየግጥሞቹን ሁኔታ መልክ ማግ ኘቱ ላይ ነው ። ሕዝባዊ ግጥሞች በየሰው አንደበት በተለያዩ ጊዜያት በሚነገሩበት ወቅት አንዳንድ ለውጦችን እያደረጉ ፤ በይዘታቸውም ላይ እያከሉ ወይም እየቀነሱ መሄዳቸው እርግጥ ነው ። አንድ ምሳሌ እንውሰድ ። አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ውሁድነት በመሻት በሚታ ክቱበት ሰዓት እንደሌላው አውራጃ ሕዝብ ሁሉ የጐንደርም ሕዝብ ሸፍቶባቸው ሲዘምቱ አንድ ፫፻ ሰው ሲሸሽ ይደርሱና ወንድ ወን ዱን ገድለው ሴት ሴቱን ይተውታል ። (2) በዚያን ጊዜ አንዲት አልቃሽ

አንጥረኛው ብዙ በቴዎድሮስ ቤት
ባላልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት ።

ስትል ታለቅሳለች ። ይህ ባለ ሁለት ስንኝ እንጉርጉሮ ዛሬ እንደምና ውቀው ፣ በኋላ ይሁን በፊት የአንድ ቃል ለውጥ አምጥቶ እናያለን ።

አንጥረኛው ብዙ በንጉሡ ቤት
ባላልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት ።

ይህ የአንድ ቃል ለውጥ /በሰዋስው መንገድ ከተጸውዖ ስም ወደ ወል ስም/ ሌላ ዓይነት ለውጥን ያስከትላል ፡- በይዘት ረገድ ። የመጀመሪያው አንድ የተወሰነ 'ቴዎድሮስ' የሚባል ንጉሥን አድራጐት ሲገልጽ ሁለተኛው እንደ ቴዎድሮስ «የጭካኔ» ሥራን ለሚያካሂድ ንጉሥ ሁሉ ሊውል ይችላል ። ስለዚህ ለተለየ ሰው እናም ምናልባት ለተለየ ዘመንና ቦታ ፤ ግን ለተመሣሣይ ድርጊት ሊውል እንደበቃ ለመገንዘብ ያሻል ። ከዚሁ የአንድን ሕዝባዊ ግጥም ሃሌታ መልክ ከማወቅ ችግር ጋር የተያያዘ ሌላው ችግር ግጥሙ የተደረሰበትን ዘመን ለማወቅ ሲሞከር የሚመጣው ችግር ነው ። ምንም እንኳን የቴዎድሮስን ስም የሚጠራው ግጥም የተደረሰበትን /ወይም የተባለበትን/ ዘመንና ቦታ ለማወቅ ባያስቸግር ፤ በሁለተኛ መልኩ ባለበት ሁኔታ ግን መችና የት እንደተባለ መለየቱ ያዳግታል ። የግጥሙ ሁለተኛ ያልነው መልክ ባፍራሹ የመጀመሪያ ካልነውም ቀድሞ የተደረሰ ሊሆን ይችላል ። አልቃሿ ከቀደመ ትውልድ የወረሰችውን ግጥም ቴዎድሮስን በሚመለከት መንገድ አጥብባ ተገልግላበትም ይሆናል ። ብቻ ሕዝባዊ ሥነግጥም ሕያው ሥነ ጽሑፍ በመሆኑ - ማለትም በወረቀት ሠፍሮ ፡ ቋሚ መልክ ይዞ - በደራሲው ነጠላ ሰረዝና ሙሉ ነጥብ ተቀንብቦ የሚቆይ ነገር አይደለምና ፤ ይህ ግጥም የዚህ ዘመን፣ የዚህ ቦታ ሕዝባዊ ግጥም ነው ብሎ በእቅጩ መወሰን ብዙ ጊዜ ቀላል አይሆንም ።

ሕዝባዊ ሥነ ግጥም የአንድ የተወሰነ የማኅበረሰብ ክፍል ብቸኛ ሀብት አይደለም ። ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ይፈልቃል ። ከተለያዩ መደቦች ውስጥም ይሰርጻል ። ሰፊው ሕዝብ በየዕለት ውሎ አምሽቶ በዚህ ጥበብ ሲገለገል እንደቆየ ሁሉ ፣ ከነገሥታቱ ፣ ከመኳንንቱ አንደበትም የራቀ ነገር እንዳልነበረ ብዙ የሚጠቁሙን የዚሁ ጥበብ ቅርሶች የሆኑ ማስረጃዎች አሉን ። ይሁንም የፊደልን ብርሃን ሣያዩ ለቆዩት ብዙኀን በይበልጥ ፣ የብሶትና የሀሴት መግለጫቸው ሁኖ ቆይቷል ። ለምሣሌ ፣ በታህታይ መደቦች አባላት አንደበት ሲነገር የቆየውን የመጨቆንን መራራነት ፣ የብሶትን እሬትነት የሚገልጡትን ቀጥሎ ያሉትን አራት ስንኞች ማን ይዘነጋቸዋል ?

እግዜርና ንጉሥ ተጣልተው ቆመው
ቅዱስ ሚካኤልን ዳኛ አስቀምጠው
እግዜር በግራ ነው ንጉሡ በቀኝ
በል ፍጅና ስጠኝ ሲለው ሰማሁኝ ።

ስለ ሕዝባዊ ሥነ ግጥም ስንናገር «ከብዙ በጥቂቱ» ብለን ብን ጀምር የተሰለቸ ሐረግ መድገም አይባልም ። እና «ከብዙ በጥቂቱ» ብለን በመጀመር ለአብነት ያህል ብቻ አንዳንድ ልዩ ልዩ ይዘቶች ያሏቸውን ግጥሞች እንጠቅስና እንወያያለን ። የባህል ይዘት ባላቸው አያሌ መጻሕፍት ውስጥ በገፍ የሚገኙትን የፉከራ ፣ የበዓላት ፣ የፍ ቅር ፣ የኀዘን … ወዘተ. ግጥሞችን ሆን ብለን ትተናቸዋል ። ለጊዜውም ቢሆን ።

## ሀ <u>ታሪካዊ ነቁጦችን የያዙ ሕዝባዊ ግጥሞች</u>

1. እህል በፊት ሲሸሽ በሬ ሲያባርር
ሁሉም ተከታትለው ጠፉ አሉ ካገር ።

ይህ ሁለት ስንኝ ግጥም የተደረሰው በ፲፰፻፹፩ በሀገሪቱ ላይ የከብት እልቂት ደርሶ ፣ ከሦስት ዓመት በኋላም ታላቅ ደዌ ገብቶ ሕዝብ በጨረሰበት ጊዜ ነበር - በክፉ ቀን (3) ። ያልታወቀው ደራሲ ጥልቅ በሆነ መንገድ በከብት እልቂትና በደዌው ምክንያት በሀገሪቱ ላይ ደርሶ የነበረውን ረሀብ ገልጦታል ። ግጥሙ በሰምና ወርቅ መን ገድ የተከወነም ባይሆን ፣ በእያዎ /*paradox*/ የዘይቤ ስልት የተ ቀመረ ነው ። የመጀመሪያውን መስመር መልከት እንዳደረግን መልእ ክቱ በቶሎ ሳይገባን ይቆያል ። የእህልና የበሬ መባረር እንግዳ ነገር ይሆንብናል ። የአንዱ መኖር የሌላኛውም መኖር ነው ብለን ከየዕለት ገጠመኞችን ስለምንረዳ ። ዝግ ብለን ነገሩን ስናሰላው ግን በአገላለጹ 'እንግዳ' ግራቢስ ጠባይ መሠረትነት እውነትነቱ እየተሰማን ይሄዳል ። ያልታወቀው ደራሲ የተጠቀመበት የሰዋስው አገባብ አባራሪውንና ተባራሪውን እንኳ ባፋጣኝ ለይቶ ግልጽ በሆነ መንገድ አያሳየውም ። እንደ ነገሩም ቢሆን አጠራጣሪነት /*ambiguity*/ አለው ። ይህም አጠራጣሪነቱ የግጥሙ ውበት ሁኖ ፣ ጉልበቱ ፤ ዘግይቶም የሚገባን ግልጽነቱ ፣ የበሬውንና የእህሉን ተደጋጋፊ ሕይወት ገጣሚው አጽን ዖት የሰጠበትን ኪኑን እንድናደንቅለት ያደርገናል ።

2 አጼ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ
የሸዋን መኳንንት እጅ ነስተውት ሄዱ ።
ባለድባብ ንጉሥ ባለጥና አበውን
እየዞሩ ፈቷት ኢትዮጵያን ።

ይህ ግጥም የተገጠመው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ጊዜ እንደነበረ ግልጽ ነው ። አፄ ቴዎድሮስ በየመሣፍንቱ እጅ ተከፋፍላ የነበረችውን ኢትዮጵያ አንድ ለማድረግ በየቦታው እየዘመቱ ፣ በታ

ናናሽ ንጉሦች ላይ ድል እያገኙ ቆይተው ሳለ ፣ የያዟቸው አውራጃ ዎች ሕዝቦች በየድንገት በቀል አምባ ገነን መሣፍንት እየተቀሰቀሱ እንደገና ያምጹባቸው ነበር ። አቤቶ ሰይፉ እሚባሉ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ወንድም ፣ አፄ ቴዎድሮስ ሸዋን ድል አድርገው በሾሟቸው አቶ በዛብህ ላይ አምጸው ተነሱ ። አንኮበር ድረስ ዘልቀውም አቶ በዛብህን አባረው በሸዋ አልጋ ተቀመጡ ። ይህን የሰሙት አፄ ቴዎ ድሮስ ተበሳጭተው አቤቶ ሰይፉን ለመውጋት ወደ ሸዋ መጡ ። ከፍ ያለ ጦርነት ካደረጉም በኋላ አቤቶ ሰይፉን ድል አድርገው ፣ በአቤቶ ሰይፉም የጦር አበጋዝነት ስር የተሰለፈውን የሸዋ ሕዝብ በምርኮ ካንበረከኩት በኋላ እጅግ ኢግሩን እያስቆረጡ ጣሉት ። ፋ እንግዲህ ከላይ የተጠቀሰው ባለአራት መስመር /ሰንኝ/ ግጥም የመገጠሙ ምክንያት ይህ ታሪካዊ ሁኔታ መሆኑ ነው ። ግጥሙን በሁለት አንጓ መክፈል ይቻ ላል።የመጀመሪያዎቹን ሁለት ስንኞች እንደ አንድ የታችኞቹን ሁለት መስመሮች ደግሞ እንደሌላ አንድ። የዚህም ምክንያቱ ምንም እንኳን ግጥሙ በይዘት በኩል ያው የአፄ ቴዎድሮስን የወቅቱን አድ ራጎት የሚገልጽም ቢሆን አራቱ መስመሮች ሁለት ራሣቸውን በቻሉ የምርምር ቅኔዎች ወይም ፍቅረ ድንግል በየነ እንደሚለው 'ተቀጽላ ቅኔዎች 5 መንገድ የተጻፉ ግጥሞች ሊወጣቸው ስለሚችል ነው ። በመ ጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች፤ 'ምነዋ አፄ ቴዎድሮስ፤ ንጉሥ ሁነው መዋረዳቸው ምነዋ ከሸዋ መኳንንት እጅ መንሣታቸው? በሚል ጥላ ስር ግዘፍ ነስቶ ለዐይነ ኅሊናችን የሚቀርበው ጉዳይ "እጅ ነስተው" ከሚለው ሐረግ ውስጥ ተፈልቅቆ የሚወጣው የታሪክ ሐቅ ነው ። ይህም የታሪክ ሀቅ ቀደም ብለን በዝርው የገለጽነው ጉዳይ ነው ። የተቀሩት ሁለት ስንኞችም የቴዎድሮስን ክርስቲያናዊ ንጉሥነት — አቡንነት የሚነግሩን መስለው እየዞሩ ፈቷት በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን የቴዎድሮስን ሀገር ፈችነት /አጥፊነት/ ከዚሁም ጋር አሸናፊነት/ ይነግሩናል።

ከላይ እንደተጠቀሱት ያሉ አያሌ የታሪክ ነቁጦችን የያዙ የአ ማርኛ ሕዝባዊ ግጥሞች አሉ። ብዙዎቹ የተጸፉት በምርምር ቅኔ ኪን ነው። የምርምር ቅኔ የሚሆነው አንዱ ቃል በሁለት /ወይም አንዳንዴ ከዚያ በላይ/ በሆኑ የትርጉም መስመሮች በመሄዱ ብቻ ሳይሆን ያ ቃል አንድም የግሥ ክፍል የሆነ እንደሆነ ወይም ይኸንኑ ቃል 'ወዲያና ወዲህ በማማታት ግዕዙን ወደአማርኛ፤ አማርኛውን ወደግዕዝ አዛውሮ እያንዳንዱን ቃል ከፋፍሎና መላልሶ ሲያዩትና ፍች ይዞ ሲገኝ ነው ። ከላይ የተነተናቸው ነስተውት እና ፈቷት የተሰኙት ቃላት ለዚህ መል ካም አብነት ሊሆኑን ይችላሉ። ሌሎች አያሌ የታሪክ ይዘት ያላቸው

የአማርኛ ሕዝባዊ ግጥሞች በኅብር መንገድ ተጽፈው እናገኛለን ። ኅብር ፤ እንደምርምር ሁሉ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ትር ጉሞችን ሊይዝ ቢችልም ፤ የግሥ ክፍል ሳይሆን የስም ክፍል ነው ። ቀደም ብለን የጠቀስናቸው አቤቶ ሰይፉ በሞቱበት ጊዜ የተገጠመ እንድን ባለሁለት ስንኝ ግጥም ወስደን ብናይ የኅብርን ምንነት በቀ ላሉ መረዳት እንችላለን ።

3. የሸዋ መኳንንት እንግዲህ አትልፉ
ተመዞ የነበረ ተከተተ ሰይፉ ።

ተመዞ የነበረ ተከተተ ሰይፉ ሲል መጀመሪያ በዐይነ ኅሊናችን የሚመጣው ስዕል ላጥ ተደርጎ የነበር የተባ ሰይፍ ወደአፎቱ መከተ ቱን ነው። ቆይተን ግን ሰይፉ የሚለው ቃል ላይ አስተውሎታችንን ገታ ስናደርግ የአቤቱ ሰይፉን ሞት እንረዳለን። እንግዲህ አንድ ቃል /ስም—በሰዋስው መንገድ/ ሁለት ፍቺ ሲኖረው ይህን ይመስላል ማለት ነው ።

ለ/ <u>የአደን ግጥሞች /ጉሮ ወሸባዬ ግጥሞች/</u>

በሀገራችን ውስጥ ባሉ ብዙ ብሔረሰቦች ባህል መሠረት የዱር አውሬ አደን ከፍተኛ ግምት ሲሰጠው የቆየ ነገር ነው። ወጣቶች ለአ ካለ መጠን መድረሳቸውን የሚያስመሰክሩበት ፤ በመካከለኛ ዕድሜ ያሉ ሰዎችም ሆኑ ጠና ያሉቱ ጉልበታቸው አለመላሙን እሚያሳዩበት በዚህም በማኅበረሰቡ ውስጥ የተከበረ ወንበር እሚይዙበት አንዱ መንገድ አደን ወጥተው በለስ ቀንቷቸው የተመለሱ እንደሆን ነበር ፣ ብላታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል እንደሚሉት በለስ ያልቀናቸው ሳይገድሉ መመለስን ከትልቅ ውርደት ቆጥረው በዱር ሲንከራተቱ አንዳንድ ጊዜ ወባ ወይም ያልታወቀ የበረሀ በሽታ ይይዛቸውና ከሞት ይደርሳሉ ። (3) እንግዲህ በነበረው ማኅበረሰብ ይህን ያህል ከፍተኛ ዕሴት ይሰጠው ለነበረው የአደን ጉዞ ምን ያህል ደማቅ የኪነት አጀብ ያሻውና ይደረግለትም እንደነበር መገመቱ አስቸጋሪ አይሆንም ። አዳኙ ወደ ዘመቻው ሲሄድና ከዘመቻውም በለስ ቀንቶት ሲመለስ ፤ ከዚያም በየሠርጉና በየበዓላቱ ላይ ድሎቹንና አንዳንዴም ድክመቶቹን እሚያወሱ አያሌ የጉሮ ወሸባዬ ግጥሞች ይጉርፉለት ነበር ።
ከዚህ ከአደን ባህል መንሠራፋት አንጻር ዛሬ በቅርስነት ያገኘናቸውን ግጥሞች አነስተኛነት በዐይነትም በመጠንም/ ስናይ አያሌ ግጥሞች ባለፉ ዘመናት ማኅደራት ተቆልፈው— ምናልባትም እስከመጨረሻው ሚሽሸውና ጠፍተው— በመሆኑም ዛሬ በእጃችን የሚገኙትን ርዝራዥ

ግጥሞች ወስደን ለመመርመር ስንነሣ ስለጉሮ ወሸባዬ ግጥሞች አጠቃላይ አስተያየቶችን ለመስጠት ፍርሃት ሳይገባን አይቀርም ። ይሁን እንጂ ግን ፤ እነዚህኑ በእጃችን ያሉትን ካልመረመርን የነሱም ዕድሜ የሚያጠያይቅ ይሆናልና በነሱው ላይ አንዳንድ ሀሳቦችን ወደ መወራወሩ እናመራለን ።

1. እስቲ እንዳሻው ባቦ እንዳለ ያርገኝ
በቀጭኔ ደጋን የሚያስነድፈኝ
ምነው ብኰራ ምነው ቢጀነነኝ
ቀጭኔ ተጋዳይ ያገኘሁ እኔ ነኝ ።

ይህ ግጥም የቀጭኔ ገዳይ ሚስት ያወረደችው መሆን አለበት የቀጭኔ ገዳይ በማኅበረሰቡ ውስጥ ለራሱ ከፍተኛ ግምት ከሚሰጠው ሌላ ፤ ሴቶች ወደምንጭ ወርደው ውሀ ለመቅዳት በሚጣደፉበት ጊዜ ለዚሁ— ለቀጭኔ ገዳይ ሚስት ቅድሚያ ይሰጣት ነበር ይባላል ። ለዚህ ይሆናል ምነዋ ብኰራ ምነው ቢጀነነኝ ያለችው ። በማኅበረሰቡ ውስጥ የክብር ቦታ ለማግኘት መቻሏ እንደልቧ ሳያናግራት አልቀረም ። ግጥሙ ከፍት ነው፤ ዝርው። የቅኔ ቀርቶ የዘይቤ ወይ የስለምን ጠባይ እንኳን ጉልቶ አይታይበትም ። መልእክቱ ላይ ለመድረስ ግጥሙ በተገጠመበት ፤ ከዚያም በኋላ ይኸው ግጥም በየጊዜው ይወርድ በነበረበት ጊዜ ሁሉ የነበረው ማኅበረሰብ ለቀጭኔ ገዳይ ይሰጠው የነበረውን ክብር ፤ ማወቅን ብቻ ነው እሚያጠይቅ ።

2. ምኑ ተያዘና ሸዋ ሊወጣ ነው
ለሚስቱ ቀጭኔ ለሱ ሎቲ የለው ።

አደን የተከበረ ማኅበራዊ ዕሴት ያለው ቁም ነገር በሆነበት ቦታና ዘመን ፤ በለስ የቀናው የማለፊያ ገዳይ አንዱ ምልክቱ ጆሮው ላይ የሚንጠለጠለው ሎቲ ነበር ። እዚህ አረሆዋ የምትወቅሰው ዝኖን ወይ አውራሪስ ገድሎ ሎቲ በጆሮው ሳያንጠለጥል ፤ ወደሸዋ ወደንጉሡ አደባባይ ብቅ ሊል የከጀለውን ሰው ነው ። ግጥሙ የወል እሚባለው ነው ፤ መደበኛው ቤት ። ለማስረጃነት ከምናገኛቸውም የጉሮ ወሸባዬ ግጥሞች አብዛኞቹ የሐረግ ምጣኔያቸው ስድስት ቀለም የሆነ የወል ቤት ግጥሞች ናቸው ። የአደን ግጥም አዝማች— «የጉሮ ወሸባዬ» ስንኝም መነሻ ሐረግ ባለስድስት ቀለም ቢሆንም ፤ ዛሬ ሲዜም በምን ሰማበት ሁኔታ ሁሌም ባይሆን አንዳንዴ ወደ አምስት ቀለም ፤ ማለትም ከወል ሐረግነት ወደሰንጐ መገን ሐረግነት ሲሄድ እናስተውላለን ። አቀንቃኟ የመጀመሪያውን ሐረግ ጉሮ ወሸባዬ ብላ ትጀምርና በመድገሚያው ላይ «ዬ» ን መጥራቱ ይረዝምባትና «ባ» ላይ ትተወዋለች ።

ጉሮ ወሸባዬ» የጀግና ማወደሻ ሐረግ ነው። የሰንጐ መገን ምጣኔ ለጀ ግኖች ማሞገሻ ብቻ ነበር የሚውል የሚሉም የቀድሞ ገጣሚዎችና የግጥም ሀያስያን አሉ ። (9) /በግዕዙ ሥነ ግጥም ቢሆን ለውዳሴ እግዚአ ብሔርና ለውዳሴ ንጉሥ እሚያገለግሉ የተለዩ የሐረግ ቊጥርና ምጣ ኔዎች እንዳሉ ማለት ነው ።/ እንድ ጀግና የሚደረድራቸው የፉከራ ግጥሞችም በሰንጐ መገን ምጣኔ እንደሚሄዱ ስለምናውቅ ይህ የገጣሚዎ ቹና የሀያሲያኑ አባባል እውነት እያጣም ከሚል አዝማሚያ ላይ እን ደርሳለን ። በዚህም አንጻር ነገሩን ስናጤነውና ዛሬ ካገኘናቸው የአደን ግጥሞች አብዛኞቹ በወል ሐረግ ምጣኔ ስር የሚገቡ መሆናቸውን ስንገነዘብ ፤ ከአዝማቹ ጋር ሊሰምሩ የሚችሉ እያሌ በሰንጐ መገን ሐረግ ምጣኔ የተደረሱ የአደን ግጥሞች እንደነበሩ— ግን ዛሬ እንደጠፉ ወይም ምርምር ገና እንዳላወጣቸው እንገምታለን ። የሆነ ሆኖ አሁን ያየናቸውንና ለታሪክ ተዘክሮ በተጻፉ መጻፍሕት ውስጥ የምናገኛቸውን አንዳንድ የአደን ግጥሞች ስንመረምር ፤ የቅኔ በሰምና በወርቅ መንገድ የሚሄደው ቅኔ ቀርቶ ፤ የጐላ የዘይቤ ጠባይ እንኳን እማይታይባቸው ሌጣ ግጥሞች ሁነው ነው እምናገኝ ።

ሐ/ የችሎት ግጥሞች

ቆየት ባለው ዘመን ፤ በየችሎቱ ላይ የሚታይ አንድ ተውኔታዊ ጠባይ የነበረው ጉዳይ ነበር ። ይኸውም ፤ ዳኛው ችሎቱን ለማስቻል ዛፍ ሥር ተቀምጦ ፤ ሕዝብም ፍዝ ተመልካች ሳይሆን በተቺነት ንቁ ተሣታፊ ለመሆን አሰፍስፎ ባለበት ቦታ ከሣሽና ተከሣሽ ወይም ዘንገኞቻቸው / ጠበቆቻቸው / ከሚከራከሩበት ርዕስ ጉዳይ ራቅ ባለ ጭብጥ ላይ ግጥም እያወረዱ እርስ በርሳቸው ይበሻሸቁ ፤ እንደበተ ርቱዕነታቸውንም ይሞካከሩ ፤ ይመዛዘኑ ነበር ። ዳኛውም ከርዕስ ነገሩ ርቃችኋል ፤ ጊዜዬን አታጥፉብኝ ሳይል ፤ ይህንኑ የግጥም ውጊያ እንደ ችሎቱ ባህል አንድ ገጽ በመቁጠር ፤ በጥሞና ከማዳመጡም በላይ ፤ አልፎ አልፎም ሙሌው ዘንገኛ በሚጥልለት የግጥም እምኃ በመማለል የነገሩን ፤ የክሱን ጭብጥ በጽሞና ማንጠር እያቃተው ፍርድ የሚያዛ ባበት ወቅትም ጥቂት አልነበረም ። ባለጉዳዩ ውርዱን የሚነዛው /ይህን ዐይነቱን ግጥም በችሎት ላይ ማሰማት «ውርድ መንዛት» ነው እሚባለው ።/ ከተለመደ አባባል በመነሣት ነው ። ይህም የዚህ ዓይነቱ ግጥም አንድ ጠባይ መሆኑ ነው ። ውርድ ነገርው በቀጥታ ወደግጥሙ ከመግባቱ በፊት እንደማስጠንቀቅ አድርጐ ፤ «በላ ልበልሃ..» ብሎ ነው የሚጀምር ። የፉከከር ጥሪ ነው ፤ የ«ናልኝ» ድምፅ ። በችሎቱ ውስጥ የታደሙትን ሰዎች ልቦናና ትኩረት የመሳብ ጥሪ ።

በላ ልበልሀ....
ለፌቆ የላት ባት
ለዶሮ የላት ግት
ለቀበሮ የላት ገሳ
ለውሻ የላት ምሣ...

ይህን ካንድ በኩል የተነዛውን ውርድ ምንነት በአፋጣኝ የተረዳው በተቃራኒ የቆመው ጮሌ ዘንገኛ ገና ውርድ ነገሯ ትንፋሹን ሳይውጥ ቀበል ያደርግና መልስ መስጠት ይጀምራል ። እንዲህ ሲል ፤

በላ ልበልሃ...
ውሻ ባይኖራት ምሣ
ያን ሁሉ ጅብ መልሣ ፤
ቀበሮ ሳይኖራት ገሳ ፤
ያን ሁሉ ጉድጓድ እርቃ ምሳ ፤
ዶሮ ባይኖራት ግት
ያን ሁሉ ጫጩት አንተ አሳደክላት?
ለፌቆ ባይኖራት ባት
ያን ሁሉ ሜዳ አንተ ሮጥክላት?

ይህ የችሎት ግጥም ሁሌም ባይሆን ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለ የእንቆቅልሽነት ጠባይ ይታይበታል ። ምክንያቱም ግልጽ ነው ። ውርድ ነገሯ የሚፈልገው ባላጋራውን አደናግሮ አፉን ለማስያዝ ነው ፤ በዳኞችና በተቺዎች ዘንድ ዝቅተኛ ግምት እንዲሰጠው ። ይብሱን «ካያያዝ ይቀዳል ፤ ካነጋገር ይፈረዳል» ከዚሁ ማኅበረሰብ ውስጥ የመነጨ ምሳሌ መሆኑን ስንረዳ ውርድ ነገሯ ባላጋራውን አንደበተ ለምባዳ ለማድረግና በዚህም መነሾ ዳኝነት ለሱ እንድታደላ የሚያደርገው ጥረት ለምን ታ ይገባናል ። ውርድ ነገሯ በባላጋራው ላይ የበላይነትን ካገኘ ራሱንም ቢሆን በችሎት መሀል ለማመስገን አይመለስም ፤ ራሱንም ለማወደስ ፤ ለማን ቆላጵላጠስ ። እያለ ፤

ከኔ የተሟገተ
ከግንድ የተጓተተ
ከጤፍ ቆረን የቧገተ ፤
ከኔ የተጣላ
ጥንጣን የበላው ባላ ፤
ከኔ መሟገት
ከድንጋይ መማከት ።

የችሎት ግጥም ፤ የቅኔነት ጠባይ ባይታይበትም በውብ ዘይቤዎች የተመላ ነው። ከላይ የጠቀስነው ውርድ ነገር «ከኔ የተጣላ ፤ ጥንጣን የበላው ባላ» ሲል «ጥንጣን የበላው ባላ» በሚለው ተለዋጭ ዘይቤ አማ ካይነት ከሱ ጋር ተከራክሮ መርታት ምን ያህል ከንቱና የማይሞከር ፤ ቢሞከርም የማያዋጣ እርምጃ እንደሆነ ለባላጋራው በደመቀ የንግግር ስዕል ገልጾለታል ። የችሎት ግጥም አንድ ዓይነት የሐረግ ምጣኔ የለውም ። በተለያዩ ሐረጎች ለምሳሌም በወል ፤ በቡሄ በሉ በሰንጐ መገን ሐረግ ሊሄድ ይችላል ። ሐረጉ እንደ ስንኝ አንድ መስመር የሚይዝበትም ጊዜ አለመገደዱን ከላይ በተጠቀሱት ግጥሞች ውስጥ መለየት ይቻላል ።

እንግዲህ ያማርኛን ሕዝባዊ ሥነ ግጥም እንዲህ ጐረፍ ጐረፍ አድርገን ለአብነት ያህል ካየን እዚሁ ላይ እንቀንተው ። ብዙ የምር ምር ሥራን ገና የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ለምሁራን ሊያሳስብልን ከቻለ በቂ ነው ። ሕዝባዊው ሥነ ግጥም ሕዝቡ በየዕለት ውሎው ለሚ ያጋጥመው የኀዘን ፤ የደስታ ፤ የፍቅር ስሜቶች መግለጫ በመሆን አገ ልግሏል ። በየበዓላቱ የሚሰሙት የ«ሆያ ሆዬ» የ«ከብረው ይቆዩኝ» ግጥሞች ሁሉ በዚሁ ዐቢይ ሥነ ግጥም ውስጥ እሚጠቃለሉ ናቸው ። እረኞች በየጐራው ላይ ፤ ቃልቾች በየመጅሊሱ ላይ ሲያወርዷቸው የቆ ዩት ትንቢት አዘል ግጥሞች በተቻለ መጠን ሊሰበሰቡና ሊጠኑ እሚ ገባቸው የዚሁ የሕዝባዊው ሥነ ግጥም አንድ አካል ናቸው ። የሕጻናት ግጥሞች / nursery rhymes / ቢሆኑም ከዚህ የሥነ ጽሑፍ ዐይነት የሚወጡ አይደሉም ።

## የግርጌ ማስታወሻዎች


1 Hailu Araya. Ethiopian Folk Poetry; Recreated (Addis Ababa University Press, 1978). p. 3

2 ተክለጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ /ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1964/ ገጽ 30

3 icard Pankhurst. Economic History of Ethiopia1800 - 1935 (Addis Ababa University Press, 1968) p. 167

4 ተክለጻድቅ ፤ ጥቁም ሥራ ፤ ገጽ 16

5 ፍቅረ ድንግል በየነ ፤ የሥዕላዊ ንግግሮች ሰዋስው /በእስቴንስል የተባዛ 1971/ ገጽ 155

6 ዓለማየሁ ሞገስ ፤ የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ ፤ /ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤ 1954/ ገጽ 65

7 ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል ፤ ዝክረ ነገር ፤ /ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤ 1962/ ገጽ 341

8 ዝኒከማሁ ፤ ገጽ 445

9 ዓለማየሁ ፤ ጥቁም ሥራ ፤ ገጽ 16